# ደንብ

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

**ተዛማጅ ጽሁፎች** ACA, ACF, ACI, ACF-RA, BFA, CNA-RA, CNA-RB, COG-RA, ECC-RA, EGF-RB, EGI-RA, IGN, IGO-RA, IGP-RA, IGT-RA, IKA-RA, IKB-RA, IKC-RA, IOE-RA, IOE-RB, IOI-RA, IPD-RA, IQB-RA, IQD, IQD-RA, IQD-RB, JEA, JEA-RA, JEA-RD, JEE, JEE-RA, JEC-RA, JFA, JGA, JGA-RA, JGA-RB, JGA-RC, JGB-RA, JHF, JHF-RA, JOA-RA, JPC-RA, JPD-RD, KBA-RC, KEA, KEA-RA, KLA-RA

**የሚመለከታቸው ጽ/ቤቶች፡-** የምክትል ሱፐርኢንተንደንት ጽ/ቤት፣ የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ደህንነት ኃላፊ ጽ/ቤት፣ የስትራቴጂክ ኢንሼቲቭስ ኃላፊ ጽ/ቤት

## የተማሪ መብቶችና ሃላፊነቶች

**I. አላማ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ JFA የመተግበር ሂደቶችን ለማስገንዘብ ስለ ተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች

**II. የመነሻ ታሪክ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች የዴሞክራሲያዊ ህብረተሰብ ጥልቅ ግንዘቤና ማድነቅ እንዲችሉ ስለ መብቶቻቸውና ሃላፊነቶቻቸው በጥራትና በግልጽ ግንዛቤ ሊሰጣቸው ይገባል። ተማሪዎች መብቶቻቸውን በሚጠቀሙባቸው እና እንደ ዜጋ ኃላፊነታቸውን በሚወጡባቸው እድሎች ውስጥ ይህን ጥልቅ አድናቆት ያዳብራሉ።

**III. ትርጉም**

A. ጉልበት ወይም ሥልጣን ተጠቅሞ ማጥቃት/መጨቆን፣ ጥቃት/ትንኮሳ፣ ማስፈራራት MCPS ደንብ JHF-RA ላይ እንደተገለጸው ተማሪጉልበት ወይም ሥልጣን ተጠቅሞ ማጥቃት/መጨቆን፣ ጥቃት/ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት።

B. የሳይበር ጥቃት/Cyberbullying MCPS ደንብ JHF-RA ላይ እንደተገለጸው ጉልበት ወይም ሥልጣን ተጠቅሞ ማጥቃት/መጨቆን፣ ጥቃት/ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት ማለት ነው።

C. ስለ ኤሌክትሮኒክስ ኮሙኒኬሽንMCPS ደንብ JHF-RA ላይ ተብራርቷል፣የተማሪ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት

D. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ማለት፡- ባለቤትነታቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሆኑ ወይም MCPS የሚያስተዳድራቸው መሬትን ጨምሮ ማንኛውም የ MCPS ትምህርት ቤት ወይም ሌላ መገልገያ፣ የ MCPS አውቶቡሶችና ሌሎች የ MCPS ተሽከርካሪዎች፣ እና MCPS ስፖንሰር የሚያደርጋቸው ማንኛውም የተማሪዎች እንቅስቃሴ መገልገያዎች እና/ወይም ቦታዎች ናቸው።

E. ወላጅ/አሳዳጊ የተፈጥሮ ወላጅ፣ በጉዲፈቻ አሳዳጊ ወይም እንደ ልጁ ወላጅ ሆኖ/ና እንዲሰራ/እንድትሰራ ስልጣን የተሰጠው/ጣት ህጋዊ አሳዳጊ፣ ወይም በተለምዶ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በተፈጥሮ ወይም በአሳዳጊ ወላጅ ምትክ ለተማሪው(ዋ) የትምህርት ጉዳይን በሚመለከት ውሳኔ ለመስጠት በህጋዊ መንገድ ሀላፊነት ለመውሰድ የተሰየመ(ች) ግለሰብ ማለት ነው።

F. ርዕሰ መምህር ለዚህ ደንብ ዓላማ ሲባል ርእሰመምህር ወይም ተወካይ ለማለት ነው።

G. ምክንያታዊ እምነትከእውነታ በመነሳት ከምክንያታዊ ግምቶች ጋር የተወሰዱ የተወሰኑ እና ገላጭ እውነታዎች ጋር የተገኘ እምነት ነው።

H. ማጨስ MCPS ደንብ IGO-RA፣ የአልኮሆል፣ የካናቢስ፣ የትምባሆ እና ሌሎች ተማሪዎችን የሚያካትቱ አደንዛዥ ዕፆችን አላግባብ የመጠቀም ክስተቶች መመሪያ፣ COF-RA፣ አልኮል፣ ትምባሆ እና ሌሎች መድሃኒቶች MCPS ንብረት ላይ፣ እና MCPS ውስጥ የተማሪ የሥነ ምግባር ደንብ ላይ ትርጉም ተሰጥቶታል።

## IV. የአፈጻፀም ቅደም-ተከተሎች

A. ነፃ ህዝባዊ ትምህርት

1. በትምህርት ቦርድ ፖሊሲ JEA ላይ እንደተገለፀው፣ ነዋሪነት፣ የትምህርት ክፍያ፣ እና ምዝገባ ብቁ የሆኑ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎች በሕዝብ ትምህርት ቤቶች ያለክፍያ የመማር መብት አላቸው።[1]

2. የአካል ስንክልና ያላቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎች ከትውልድ ቀን ጀምሮ የተማሪው(ዋ) እድሜ 21 አመት በሚሞላበት የትምህርት አመት መጨረሻ ድረስ ተገቢ ህዝባዊ ትምህርት በነፃ የመማር መብት አላቸው።

B. በመማርና በት/ቤት ሥራዎች ላይ የተማሪዎች ተሳትፎ

1. ተማሪዎች የእያንዳንዱ ኮርስ አጠቃላይ ዓላማዎች እና አፈፃፀማቸው ምንን መሰረት አድርጎ እንደሚገመገም ይነገራቸዋል። ተማሪዎች በትምህርት ክፍል እንቅስቃሴዎች ላይ የመሳተፍና ለትምህርት ክፍል ደንቦች፣ ግዴታዎች፣ እና የአሠራር ሂደቶችን የመታዘዝና የማክበር ሃላፊነት አለባቸው።

2. ት/ቤቶች ለመማር ሰላማዊ ቦታዎች ይሆኑ ዘንድ ተማሪዎች ከማሸማቀቅ፣ ከወከባ፣ ወይም ከማስፈራራት ነፃ በሆነ ኣካባቢ የመማር መብት ኣላቸው። ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ለመማር እንቅፋት ከመፍጠሩም በላይ በአካዴሚያዊ ክንውን፣ በስሜታዊ ደህንነት፣ እና በት/ቤት ድባብ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያስከትል ይችላል። የማሸማቀቅ፣ የትንኮሳ፣ ወይም የማስፈራራት ክስተቶችን ሪፖርት ማድረጊያ ሂደቶች MCPS ደንብ JHF-RA፣ የተማሪ ማሸማቀቅ፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት በሚለው ላይ ተገልፀዋል።

3. ተማሪ-የሚፈልጋቸው የትምህርት ፕሮግራሞች

ተማሪዎች፣ ከፋከልቲ (የት/ቤት አስተዳደር) ጋር በመመካከር በተመረጡ ርእሶች ላይ ሴሚናሮችን፣ ስብሰባዎችን፣ ወይም ኣጫጭር የጥናት ኮርሶችን በትምህርት ቀን እንደ አማራጭ

[1] 4 ዓመት የሞላቸው እና የቤተሰባቸው ገቢ መስፈርቱን የሚያሟላ ልጆች በህዝብ ቅድመ-ትምህርት ቤት ያለ ክፍያ የመማር መብት ኣላቸው።

ኮርስ ወይም ለመደበኛ ፕሮግራም ተጨማሪ እና/ወይም ከትምህርት ቀን ውጭ የሚከናወን የተማሪዎች የበጎ-ፈቃድ ተፈላጊ ፕሮግራሞች ሃሳብ ማቅረብ ይችላሉ።

a) ተማሪዎች ፕሮግራሞችን ለማቀድ ከርእሰመምህራንና ከሰራተኞች ጋር በመተባበር ይሰራሉ።

b) ፕሮግራሞች ከዲስትሪክቱ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ስልታዊ ጉዳዮች እና ከ MCPS ትምህርታዊ ተልእኮ ጋር የሚጣጣሙ፣ ለታዳሚው ዕድሜ እና ብስለት የሚመጥኑ፣ እና አወዛጋቢ ርዕሰ ጉዳዮችን በማቅረብ ረገድ ሚዛናዊነትን ለመፍጠር የተዋቀሩ መሆን አለባቸው።

4. ፖሊሲዎች እና ደንቦች

a) ከቦርድ ፖሊሲ BFA፣ የፖሊሲ ቅንብር ጋር በሚጣጣም መልኩ የተማሪዎች ተወካይ ተማሪዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ዋና ዋና የቦርድ ፖሊሲዎችን በማሻሻል ወይም በማዘጋጀት ላይ መሳተፍ አለባቸው። እንደዚህ አይነት ተሳትፎ በሚመለከተው ጽ/ቤት፣ መምሪያ ወይም ኮሚቴ፣ በስብሰባዎች ውስጥ የተማሪዎችን ተወካይ ጨምሮ ወይም የተማሪዎችን ግብዓት በመጠየቅ በማዘጋጀት ወይም በክለሳ ሂደት ካሉት በርካታ ደረጃዎች ውስጥ በማንኛውም ሊከናወን ይችላል።

b) ተማሪዎች በአካባቢ ት/ቤት ዋና ዋና መመርያዎች ወይም በተማሪዎች ላይ ተፅእኖ በሚያሳድሩ ደንቦች ክለሳ ወይም ዝግጅት ላይ ተመሳሳይ የመሳተፍ መብት ይኖራቸዋል።

c) ተማሪዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ አበይት የአካባቢ ትምህርት ቤት መመርያዎች ወይም ደንቦች ከመዘጋጀታቸው ወይም ከመከለሳቸው በፊት ለተማሪዎቹ ምቹ በሆኑ ቦታዎች ላይ በመለጠፍ እና ከተማሪዎች ለሚሰጡ አስተያየቶች በቂ ጊዜ በመስጠት፣ ተማሪዎች እንዲገመግሟቸው ቅጂዎቹ ተደራሽ ይደረጋሉ። የሥራ ባልደረቦች ማናቸውንም በተማሪዎች ላይ ተፅእኖ በሚያደርጉ የአካባቢ ት/ቤት መመርያዎች ወይም ደንቦች ላይ በተገኙ እድሎች ከተማሪዎች ጋር እንዲወያዩባቸው እና እንደአስፈላጊነቱ መረጃና ማብራርያ እንዲሰጡ ይበረታታሉ።

d) ተማሪዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ አበይት ፖሊሲዎችን እና ደንቦችን በማዘጋጀት ወይም በመከለስ ላይ ግብአት ለማቅረብ የሚፈልጉ ተማሪዎች ርእሰመምህራቸውን ወይም ዳይሬክተሩን፣ የተማሪ አመራር እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን የሚከታተለውን ክፍል ማነጋገር አለባቸው።

C. የብህትውነት መብቶች

1. ተማሪዎች በቤተሰብ የተፈጠሩ ክስተቶችን ወይም ግላዊ ልማዶችን፣ግንኙነቶችን፣ምርጫዎችን፣ ባህሪያትን፣ ውሳኔዎችን ወይም ችግሮችን የሚመለከቱ ግላዊ መረጃዎችን ሳይገልጹ ወይም እራሳቸውን ወይም ቤተሰቦቻቸውን ከሌሎች ጋር ሳያወዳድሩ በክፍል ውይይት፣ በቤት/በክፍል ስራ ወይም በሌላ መንገድ የማስተማሪያ/የትምህርት ዓላማዎችን የማሟላት መብት አላቸው።

2. ተማሪዎች በት/ቤት የኮምፒውተሮች አጠቃቀም ላይ ግላዊነትን የማስጠበቅ መብት የላቸውም። ተማሪዎች MCPS ደምብ IGT-RA፣ ስለ ኮምፒውተር ሲስተሞች፣ በኤሌክትሮኒክስ የሚተላለፉ መረጃዎች፣ እና የበይነ-መረብ ደህንነት የተጠቃሚ ሃላፊነቶች እና COG-RAየግል ተንቀሳቃሽ

(ሞባይል) መገልገያዎች እና ሌሎችንም የኤሌክትሮኒክስ ግንኙነትን በሚመለከት አግባብነት ያላቸው ህጎችን እና ገደቦችን ደንብ የማክበርና የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው።

3. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አውቶቡሶችን ጨምሮ፣ የተለጠፈ ማስታወቂያ ባላቸው MCPS ንብረት ላይ ያሉ ተማሪዎች የኦዲዮ እና የቪዲዮ ካሜራ ክትትል ተጋላጭ ሊሆኑ ስለሚችል ማንኛውም ተማሪ በእንደዚህ አይነት የድምጽ ወይም የምስል ክትትል በተሰበሰበ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ የስነ-ስርዓት/የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድበ(ባ)ት ይችላል።

D. ትምህርት ላይ መገኘት/መከታተል

1. ተማሪዎች ት/ቤት እንዲከታተሉ እና ወደ ት/ቤት እና ወደ መማርያ ክፍሎች በወቅቱ እንዲደርሱ ይጠበቅባቸዋል። የተማሪ በክፍል ውስጥ መገኘትን የሚመለከቱ MCPS ደንቦች JEA-RA፣ የተማሪ በትምህርት ላይ መገኘት፣ JGA-RB፣ እገዳ እና ማባረር; JEC-RA፣ የተማሪን ከክፍል እና ከትምህርት ቤት መውጣትን እና IQB-RA፣ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን ሁሉ ያካትታሉ።

2. ተማሪዎች፣ ከትምህርት ቤት መቅረታቸው በህግ ፊት የሚኖረው ውጤት ምንም ይሁን ምን፣ MCPS ደንብ IKA-RA፣ የውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት አቀራረብ መሰረት፣ያመለጧቸውን ስራዎች የማካካስ ሃላፊነት አለባቸው እና እንዲያካክሱ ይጠበቃሉ። እንዲሁም፣ MCPS ደንብ IKC-RA፣ የክፍል አማካይ ውጤቶችን (GPA) እና የተመዘኑ የክፍል አማካይ ውጤት (WGPA) ይመልከቱ።

E. የተማሪ አስተዳደር

1. ተማሪዎች የተማሪ አመራር ድርጅት ለማቋቋም እና በውስጡ የመሳተፍ መብት አላቸው። ተማሪዎች በተማሪ አመራር ድርጅት አማካኝነት በት/ቤት ጉዳዮች ድምፃቸውን የማሰማት መብት አላቸው። ተማሪዎች ውጤታማ እና ተጠያቂነቱ ለተማሪዎች የሆነ የተማሪ አመራር ድርጅት ለመፍጠር የመስራት ሃላፊነት አለባቸው።

2. ተማሪዎች፣ በተማሪ አመራሮች አማካይነት፣ለት/ቤት አስተዳደር ለቀረበ ጥያቄ በአምስት የትምህርት ቀኖች ውስጥ መልስ የማግኘት መብት አላቸው። ጥያቄዎቹ ተቀባይነት ካላገኙ ወይም ለውጥ ከተደረገባቸው የት/ቤት አስተዳደሩ በጽሁፍም ሆነ በቃል ምክንያቶችን ያቀርባል/ይሰጣል። የቀረቡት አስተያየቶች/ሃሳቦች/ጥያቄዎች ሰፊ ወይም ውስብስብ ከሆኑ፣ የት/ቤቱ አስተዳደር ከተማሪዎች አመራር ተወካዮች ጋር በመመካከር፣ የቃል ወይም የፅሁፍ መልስ የሚሰጥበትን ተቀባይነት ያለው የጊዜ ገደብ ይወስናል።

3. ተማሪዎች እንዳስፈላጊነቱ ከት/ቤት ሰራተኛ ወይም ስፖንሰር ጋር በመመካከር፣ ለተማሪ አመራር የፅሁፍ መተዳደርያ ደንብ የማዘጋጀት ወይም ባለው መተዳደርያ ደንብ ላይ ማሻሽያ የማዘጋጀት ሃላፊነት አላቸው። ሁሉም የመተዳደርያ ደንቦች የርእሰ መምህሩ(ሯ)ን የውሳኔ መስጠት ስልጣን እውቅና የሚሰጥ አንቀፅ ማካተት አለባቸው። ተማሪዎች ህግንና ፖሊሲን ካልጣሰ ወይም የሚጥስ ካልሆነ፤ ወይም በርእሰ መምህሩ/ሯ ግምት በት/ቤቱ ስኬታማ የሥራ ሂደት ላይ ጣልቃ እስካልገባ ድረስ፣ የተማሪዎች አመራር መተዳደርያ ደንቡን ወይም በደንቡ ላይ የተደረጉትን ማሻሻያዎች ርእሰ መምህሩ/ሯ እንዲያፀድቅ/እንድታፀድቅ የመጠበቅ መብት አላቸው። ያልፀደቀበት ምክንያቶች ለተማሪዎች በፅሁፍ ይገለፅላቸዋል አስተዳደራዊ ስጋቶችን አስመልክተው የመተዳደርያ ደንቡን ለመከለስ እድል መሰጠት አለባቸው።

4. MCPS ትምህርት ቤት ውስጥ በሕጋዊ መንገድ የተመዘገበ(ች) ማንኛውም ተማሪ እና በተማሪ አስተዳደር ሕግ ላይ የተቀመጠውን ማንኛውንም መስፈርት የሚያሟላ/የምታሟላ ተማሪ፣ በተማሪ አመራርነት ተወዳድሮ(ራ) ኃላፊነት መያዝ ይችላል/ትችላለች።

5. በአስተዳደሩ በተፈቀደ የተማሪ አመራር እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሳተፍ የትምህርት ጊዜዎችን የሳተ(ች) ተማሪ በፈቃድ እንደቀረ(ች) ይቆጠራል። ነገር ግን የቀረበትን ወይም የቀረችበትን ስራዎች የማካካስ ሃላፊነት ይኖረዋል/ይኖራታል።

6. የተማሪ አመራር፣ በማስተማር ሂደት ወይም በት/ቤት መደበኛ ሥራ የማደናቀፍ ጣልቃ እስካልገባ ድረስ፣ በት/ቤት መገልገያዎችን/ፋሲሊቲዎችን የመተቀም ተደራሽነት ሊኖረው ይችላል። ይህን ልዩ ፈቃድ ያለአግባብ እንዳይጠቀሙበት የተማሪ አመራር ሃላፊነት አለው።

7. የተማሪ አመራር ድርጅት ግስጋሴና ስጋቶችን በሚመለከት የተማሪ አመራር ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ የተማሪ አመራር ስፖንሰር፣ እና ርእሰመምህር በየወቅቱ ተገናኝተው ይገመግማሉ።

8. በስፕሪንግ ወራት፣ የተማሪ አመራር ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚቀጥለውን ዓመት ስፖንሰር ምደባ በሚመለከት ከርእሰመምህር ጋር በመገናኘት ይመክራል፤ እናም ስፖንሰሩ ከመሰየሙ በፊት የተማሪዎች አስተያየት ጥብቅ ግንዛቤ ይሰጠዋል።

F. የመጠየቅ እና —

1. የንግግር ነፃነት

a) ተማሪዎች የሚከተለው መብት አላቸው —

(1) በስቴት ወይም በካውንቲ የስርአተ ትምህርት ሰነዶች ላይ አወዛጋቢ የሚገድቡ ርእሶችን በሚመለከት የተለያዩ አማራጭ አስተያየቶች እንዲሰጣቸው፣

(2) እያንዳንዱን አማራጭ አስተያየት አመዛዝነው ወደራሳቸው አስተያየቶች ላይ ለመድረስ እንዲችሉ፣ እና

(3) ወደ ማጠቃለያ ከመድረሳቸው በፊት መረጃዎችን እንዲተነትኑና እንዲገመግሙ።

b) ተማሪዎች የሚከተለው ሃላፊነት አለባቸው —

(1) በኮርሳቸው የቀረቡ ርእሶችን በጥሞና እንዲያገናዝቡ እና በመማርያ ክፍል ውይይቶች በመሳተፍ በውውይት ርእሶች ላይ የተገለፁ አስተያየቶችን እንዲያዳብሩ፤

(2) የተለያዩ አስተያየቶችን እና የያንዳንዱ ግለሰብ ግላዊ አስተሳሰብ የመያዝና የመግለፅ መብትን ማክበር፤ እና

(3) አስጸያፊ፣ ነውረኛ፣ በሀሰት የሰው ስም የሚያጠፋ፣ ክብር የሌለው፣ ስነ-ስርዓት የጎደለው፣ወይም የብልግና ቋንቋን ወይም የትንኮሳ፣ የመዛት፣ የማስፈራራት ዓላማ ያለው አወንታዊ የትምህርት እና የስራ አካባቢን

የሚያደፈርስ፣ እና እርስ በርስ የመከባበር ሁኔታን ለመጠበቅ ካለው ግብ ጋር የማይጣጣም ቋንቋን ከመጠቀም ይቆጠቡ።

2. አቤቱታዎች

a) ተማሪዎች ከት/ቤት ኣስተዳዳሪዎች ጋር በመገናኘት ማናቸውንም ኣለመግባባቶች ማብራራት እና የአቤቱታ ርእስ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መረጃ የሚለዋወጡበት መድረክ የመፍጠር ሃላፊነት አለባቸው።

b) የት/ቤት ሥራዎችን እስካላደናቀፈ ድረስ፣ተማሪዎች አቤቱታዎችን ከትምህርት ክፍለጊዜ ውጭ የማሰራጨት መብት አላቸው።

c) ተማሪዎች አቤቱታዎቹ የተማሪዎችን ወይም በት/ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ የሌሎችን ጤንነትና ደህንነት ኣደጋ ላይ የሚጥሉ ተግባሮችን እንደማያበረታቱ እና አስጸያፊ፣ ነውረኛ፣ በሀሰት የሰው ስም የሚያጠፋ፣ ክብር የሌለው፣ ስነ-ስርዓት የሌለው፣ ወይም የብልግና ቋንቋ አለመሆኑን ወይም የትንኮሳ፣ የመዛት፣ የማስፈራራት ዓላማ ያለው፣ ወይም በትምህርት ቤት አሰራር ላይ ከፍተኛ ረብሻ የሚፈጥር ቋንቋን አለማካተቱን የማረጋገጥ ሀላፊነት አለባቸው።

d) በትምህርት ቤት ደረጃ፣ የሃሳቡን ጠንሳሽ መለየት ከተቻለ፣ ተማሪዎች በአምስት የትምህርት ቀናት ውስጥ ምላሹን እንደሚፈልጉ በማሳወቅ ወይም ምላሹን ለጠንሳሹ በማስተላለፍ መልስ የማግኘት መብት አላቸው።

3. ህትመቶች፣ አፈፃፀሞች፣ እና የመረጃ ቁሳቁሶች

a) ህትመት፣ እንቅስቃሴዎችን/አፈፃፀሞችን እና የመረጃ ቁሳቁሶችን በተመለከተ ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶች አሏቸው:-

(1) ተማሪዎች በት/ቤት ስፖንሰር የሚደረጉ ህትመቶችን (ለምሳሌ:- ጋዜጦች፣ ዓመታዊ መፅሔቶች፣ እና ስነፅሁፋዊ መፅሄቶች) እና በት/ቤት ስፖንሰር የሚደረጉ ትርእይቶችን (ለምሳሌ:- የት/ቤት ቲያትሮችና የቴሌቪዥን ትርእይቶች) የማምረት መብት ኣላቸው።

(2) ተማሪዎች በት/ቤት ስፖንሰር የሚደረጉ ህትመቶችንና ትርእይቶችን ይዘት ከዚህ በታች በሰፈሩት መመርያዎችና በት/ቤቱ ስፖንሰር ቁጥጥርና አመራር መሰረት የመወሰን መብት ኣላቸው።

(3) ተማሪዎች፣ ህትመቶቹን ስፖንሰር የሚያደርገው ድርጅት ወይም ግለሰብ ስም እስከተጻፈባቸው ድረስ እናም የሚሸጡት ወይም የሚሰራጩት ህትመቶች የታተሙት በ MCPS የተመዘገቡ ተማሪዎች አማካይነት እስከሆነ ድረስ፣ ያለ ት/ቤት ስፖንሰርሺፕ ህትመቶችን የማሰራጨት መብት ኣላቸው።

(4) ተማሪዎች በትምህርት ቤት ያልተደገፉ/ስፖንሰር ያልተደረጉ የተማሪ ህትመቶች ስርጭትን ለመቆጣጠር በተደነገጉ ተመሳሳይ ገደቦች እና ሂደቶች መሰረት፣ በተመደቡ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣ወይም ሌሎች በተለምዶ ማስታወቂያ ለመለጠፍ የተመደቡ ቦታዎች ላይ በትምህርት ቤት ያልተደገፉ/ስፖንሰር ያልተደረጉ ጽሁፎችን የማሳየት መብት አላቸው።

(5) በአካባቢ ት/ቤት የይግባኝ መጠየቂያ መመሪያን በመከተል ወይም ከዚህ በታች ሰክሽን F.3(f)(1) ላይ በተገለጸው መሠረት ተማሪዎች የትምህርት ቤት ስፖንሰሮችን ውሳኔ ይግባኝ የመጠየቅ መብት አላቸው። ስለ ተማሪ ይግባኝ ተጨማሪ መረጃ ከዚህ በታች በሰክሽን 0፣ ይግባኝ፣ የቅሬታ ሂደት፣ የአፈፃፀም ሒደት በሚለው ላይ ተገልጿል።

b) ስፖንሰሮች

(1) ርእሰመምህር ለያንዳንዱ በት/ቤት ስፖሰር ለሚደረግ ህትመት/ምርት የሚከተሉትን የሚያከናውን ወይም የምታከናውን ብቃት ያለው/ያላት መምህር/ስፖንሰር ይመድባል።

(a) ስለ ቁሳቁሶች ተስማሚነትና ቅርፀት መመርያ ይሰጣል/ትሰጣለች እናም ማንንም ግለሰብ የሚያንቋሽሽ/የሚጎዳ ቁሳቁስ ፈፅሞ አይፈቀድም

(b) በዚህ ደንብ ላይ የተገለጹት በተማሪዎች የተዘጋጁ ሕትመቶች፣ አፈጻጸሞች፣ እና መረጃዊ ጽሁፎችን ይዘት ስለሚቆጣጠሩ መመሪያዎች ግልጽ ግንዛቤ እንዲያገኙ ከተማሪዎቹ ጋር አብሮ የመስራት ኃላፊነት።

(2) የት/ቤት ስፖንሰሮች ለተማሪ ህትመቶች የሚከተሉትን ይፈፅማሉ፡-

(a) በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አካደሚያዊ የህትመት ማህበሮች እና በ MCPS ህጎችና ደንቦች እንዲሁም በሌሎች የጋዜጠኝነት ሙያ መመዘኛዎች ባስቀመጡት መርህ መሰረት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መመዘኛዎች መመራት

(b) በት/ቤት ጋዜጣዎች ላይ የተለያዩ አስተያየቶች መወከላቸውን እና የት/ቤቱ ማህበረሰብ አባላት በጋዜጣው ላይ አስተያየታቸውን ለመግለፅ እድል እንዳላቸው ለማየት ጥረት ማድረግ።

(3) የት/ቤት ስፖንሰሮች አንድ ተማሪ ጋዜጠኛ ያንድን ት/ቤት ወይም የቦርዱን አፊሴዬላዊ አቋም ለማራመድ ያላቸውን የሃላፊነት ሥልጣን ለማሳመን መጠቀም የለባቸውም።

አንድ ስፖንሰር በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሰናበት፣ሊታገድ፣ የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድበት፣ ወደሌላ ቦታ ሊመደብ፣ ሊዛወር፣ ወይም ሊነቀፍ አይገባም፡-

(a) በዚህ ደንብ የተፈቀደ ስነምግባርን ያሳየ(ች) አንድን ተማሪ ለመከላከል መስራት፤ ወይም

(b) በዚህ ደንብ፣ በዩናይትድ ስቴትስ ህገ መንግስት ፈርስት አሜንድመንት፣ በሜሪላንድ የሰብአዊ መብቶች አዋጅ አንቀፅ 40 ጥበቃ የሚደረግለት ስነ ምግባርን በመጣስ እምቢተኛ መሆን።

c) በተማሪዎች አማካይነት የህትመቶች ወይም ሌላ የመረጃ ቁሳቁሶች ስርጭት፡-

(1) ማንኛውም የንግድ ማስታወቂያዎችን ወይም መግለጫዎችን፣ የፖለቲካ ዘመቻ ጽሁፍን፣ እና ሃይማኖታዊ ጽሁፍን ጨምሮ የመረጃ ሰጪ ጽሁፎች ስርጭት ለሚከተሉት ድንጋጌዎች ተገዢ ናቸው፡ MCPS ደንቦች KEA-RA፣ በፖለቲካ ዘመቻዎች መሳተፍ እና የዘመቻ ጽሁፎችን ማሠራጨት፤ CNA-RA መረጃ ሰጪ ጽሁፎችን እና መግለጫዎችን መለጠፍ እና ማሰራጨት፣እና CNA-RB ማስታወቂያ።

(2) ርእሰ መምህሩ በትምህርት ቤት የሚደገፉ/ስፖንሰር የሚደረጉ እና ሌሎች በትምህርት ቤት የማይደገፉ/ስፖንሰር የማይደረጉ ህትመቶችን፣ ምርቶችን፣ ወይም ሌሎች መረጃ ሰጪ ጽሁፎችን ተማሪዎች የሚያከፋፍሉበት ጊዜ፣ ቦታ እና የሚያከፋፍሉበትን ሁኔታ መሰየም።

d) ርእሰመምህሩ(ሯ) በተማሪ የተዘጋጀውን ሥራ፣ ህትመት ወይም ሌሎች የማስታወቂያ መገልገያዎችን ማገድ፣ማስቆም፣ ወይም መከልከል የሚችለው ወይም የምትችለው በሚከተሉት መመዘኛዎች በመመርኮዝ ነው፡-

(1) ፀያፍ፣ ስም አጥፊ፣ተሳዳቢ፣ ስድ፣ ባለጌ፣ ወይም የማዋከብ፣ ዛቻ፣ ወይም የማስፈራራት ዓላማ ያለው ቋንቋ ካለበት።

(2) ያልተፈለገ የብህትውነት መብት ወረራ ሲኖረው።

(3) ተማሪዎች የሚከተሉትን ግልጽና ሊከሰት የሚችል አደጋን እንዲፈጥሩ የሚቀሰቅስ/የሚያነሳሳ ከሆነ፣

(a) ሕገ-ወጥ ድርጊት መፈጸምን፣ የቦርድ ፖሊሲዎችን እና/ወይም MCPS ደንቦችን ወይም ህጎችን የሚጥስ ከሆነ፣ ወይም

(b) የፐብሊክ ስኩልስ መደበኛ አሠራር ላይ ጉልህ ማደናቀፍ የሚያደርስ ከሆነ። "ከባድ ማስተጓጎል" ማለት፣ በት/ቤት ስራ ጣልቃ መግባት፣ ወይም በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ሥርዓት በሌለው ሁኔታ ለአመፅ መነሳሳት፣ አድሞ ከት/ቤት መቅረት፣ አድሞ መቀመጥ፣ ንብረት ማውደም፣ እና ለቆ መውጣት።

(4) የስቴት ወይም የፌደራል ህግን መጣስ። ለምሳሌ፡- ይህ በተማሪዎች ጤና እና/ወይም ደህንነት ላይ አደጋ ሊፈጥር የሚችል ወይም ተማሪዎች አደንዛዥ እፅ፣ አልኮል፣ ካናቢስ እና ትምባሆ እንዲጠቀሙ ወይም የትኛውንም ዓይነት እፅ ማጨስን፣ ጥቃትን፣ ጾታዊ ግንኙነትን፣ ህገወጥ መድልዎን ወይም ሌሎች ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን ያበረታታል/ይደግፋል ተብሎ በምክንያታዊነት ሊታሰብ የሚችል ቁሳዊ ነገርን ሊያካትት ይችላል።

ቢሆንም፣እንደነዚህ ያሉ ድርጊቶችን ኃላፊነት በተሞላበት አኳኋን ውይይት እንዳይካሄድ ለመከልከል ይህን መመሪያ መጠቀም አይገባም።

e) ማስታወቂያ

(1) ማስታወቂያ በት/ቤት ስፖንሰር በሚደረጉ ህትመቶች ወይም ድርጊቶች MCPS ደንብ CNA-RB፣የማስታወቂያ ስነምግባር እስከተከበረ ድረስ ይፈቀዳል።

(2) ተግባራዊ ማድረግ በሚቻልበት ጊዜ፣ ማስታወቂያዎች በተለየ የህትመቱ ክፍል ላይ ሲቀርቡ፣ ማስታወቂያው የአርታዒዎችን፣ የትምህርት ቤቱን ወይም የትምህርት ቦርድን አመለካከት ወይም ፖሊሲ የማያንጸባርቅ መሆኑን የሚያመለክት መግለጫ በቀዳሚነት መቅረብ አለበት።

(3) ማስታወቂያ ሊለይ የሚችል ወይም “ማስታወቂያ” ተብሎ መሰየም ያለበት ሲሆን በግለሰብ(ቦች) ስም(ሞች)፣ በኮርፖሬሽኑ ስም፣ ወይም በኮርፖሬሽንነት በህግ ተመዝግበው ያልተቋቋሙ ማኅበራት፣ ወይም ድርጅቶች ሲሆኑ፣ ማስታወቂያውን በሚደግፉት/ስፖንሰር በሚያደርጉት ኦፊሰሮች ስማቸው ተገልጾ መቅረብ አለበት።

f) የተማሪዎች የሥራ ውጤት፣ የተማሪዎች የጽሑፍ ህትመት፣ ወይም በተማሪዎች የሚደረግ የቁሳቁስ ስርጭትን የሚታገድበት ሂደት

(1) ርእሰመምህራን እገዳ ከማድረጋቸው በፊት አስፈላጊ ያልሆነ ማጓተት እንዳይፈጠር ማስረጃ የማቅረብ ሃላፊነት አለባቸው። ማንኛውም በት/ቤት ስፖንሰር የተደረገ ህትመት ወይም ክንውን፣ በሙሉ ወይም በከፊል፣ በርእሰመምህር ወይም በት/ቤት ስፖንሰር አማካኝነት ከመወገዱ ወይም ከመቋረጡ በፊት፣ ርእሰመምህር ከሚመለከታቸው ተማሪዎች ጋር በመገናኘት በሁለት ቀን ውስጥ፣ ውሳኔውን በጽሑፍ መስጠት አለበ(ባ)ት። በተቻለ መጠን የርእሰመምህሩ(ሯ) ውሳኔ ከታሰበው የህትመት ስርጭት ወይም ክንውን ከሚደረግበት ቀን በፊት ለሚመለከታቸው መድረስ አለበት። የጽሑፍ ውሳኔ ቅጂዎች ለተሳታፊዎቹ ተማሪዎች እና ለትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ቢሮ (OSSI) መሰጠት አለባቸው። ርእሰመምህሩ(ሯ) ተማሪዎችን የርእሰመምህሩ(ሯ) ውሳኔ "በሰክሽን O" ይግባኝ፣ የቅሬታ አቀራረብ ሒደት፣ ይርጋ ሂደት መሰረት ይግባኝ ሊጠየቅበት እንደሚችል ይነግራቸዋል።

(2) በትምህርት ቤት ያልተደገፈ/ስፖንሰር ያልተደረገ የጽሑፍ ህትመት ወይም መረጃ ሰጪ ጽሁፎች ስርጭትን ማስቆም ወይም በትምህርት ቤት ያልተደገፈ/ስፖንሰር ያልተደረገ ዝግጅት ክዋኔን (በመድረክ ላይ ማቅረብን) ማስቆም ለርዕሰ መምህሩ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ ርእሰመምህሩ በሁለት የትምህርት ቀናት ውስጥ ምክንያቶቹን በጽሁፍ መግለጽ ይኖርበታል፣ አንድ ግልባጭ ስርጭቱን ለሚያከናውኑ ወይም ዝግጅቱን ለሚከውኑ ተማሪዎች እና አንድ ቅጂ ለ OSSI ይሰጣል። ርእሰመምህሩ(ሯ) ተማሪዎችን የርእሰመምህሩ(ሯ) ውሳኔ "ሰክሽን O" ይግባኝ፣ የቅሬታ አቀራረብ ሒድት፣ በይርጋ ሂደት መሰረት ይግባኝ ሊደረግበት እንደሚቻል ይገልጽላቸዋል።

G. የመሰብሰብ ነፃነት

ተማሪዎች ለነሱ አሳሳቢ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ውይይት ለማድረግና በሰላማዊ መንገድ ሰልፍ ለማካሄድ የመሰብሰብ መብት አላቸው።

1. ተማሪዎች የሚከተሉትን ለመወሰን ከ ርእሰመምህር ጋር የመመካከር ሃላፊነት አለባቸው—

a) በትምህርት ቀን ተግባሩ ይፈቀድ እንደሆነ፣

b) የስብሰባዎቹ ጊዜ እና ቦታ፣ ርዕሰ መምህሩ እንቅስቃሴውን/ተግባሩን በትምህርት ሰዓት ማካሄድ በመደበኛው የትምህርት ፕሮግራም ላይ ጣልቃ ይገባል ብሎ ለማመን ምክንያት ካለ፣ እንቅስቃሴውን/ተግባሩን ከትምህርት ቀን ውጪ ወይም በምሳ ሰዓት ማድረግን/ማካሄድን ጨምሮ።

c) ምን አይነት ቁጥጥር ያስፈልግ እንደሆነ እና እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠር የትኞቹ የሥራ ባልደረቦች መመደብ እንዳለባቸው።

2. ተማሪዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው—

a) ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር በትብብር መስራት እና እንቅስቃሴው/ተግባሩ በስነ-ስርዓት መከናወኑን ለማረጋገጥ ተቀባይነት ያላቸው እርምጃዎችን መውሰድ፣ እና

b) ያመለጣቸውን የትምህርት ስራ ማካካስ።

H. ስለ አገር ወዳድነት ተግባር

1. ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶች ኣሏቸው—

a) ለሰንደቅ ዓላማ አክብሮት የመስጠትና ታማኝነትን የማረጋገጥ ሁነቶችን የሚያካትቱ ተገቢ የመከፈቻ ልምምዶች፤

b) እንደአግባቡ፣ ከስብሰባዎች በፊትና በሌሎች የት/ቤት ፕሮግራሞች ኣስቀድሞ አገር ወዳድነትን ማካተት፤

c) አወንታዊ የትምህርት ተግባሮች አካል በማድረግ ተማሪዎችን ለአገር ወዳድነት ልምዶች ማዘጋጀት፤ እና

d) በአገርወዳድነት ፐላን ዝግጅትና አመራረት መሳተፍ።

2. ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶች ኣሏቸው—

a) በኣርበኝነት ተግባር ለመሳተፍ ኣለመገደድ፣ ወይም ባለመሳተፍ ያለመቀጣት ወይም ያለመሸማቀቅ፤ እና

b) ሌሎች ተማሪዎች በአገርወዳድነት ተግባሮች ላይ የመሳተፍ መብታቸው ላይ ጣልቃ እንዳይገቡ እናም ጣልቃ የሚገቡ ከሆነ የዚህ ዓይነት ጣልቃገብነት ለዲሲፐሊን እርምጃ በቂ መነሻ ይሆናል።

I. የሃይማኖት ነፃነት

1. ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶች አሏቸው—

a) ከሃይማኖታዊ ተግባር ነፃ የሆኑ በት/ቤት ስፖንሰር የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሃይማኖታዊ ተግባሮችን አያካትቱም፤

b) በኮርሶች ወይም በት/ቤት ስፖንሰር በሚደረጉ እንደ ምረቃ ስነስርአት ወይም ስብሰባዎች የመሰሉ እንቅስቃሴዎች ሃይማኖት የማይሰበክባቸው አካዴሚያዊ አውድ፤ እና

c) የሌሎችን መብት እስካልጣሱ ወይም የትምህርት ቤት ተግባሮችን እስካላስተጓጉሉ ድረስ፣ በትምህርት ቤት የማይደገፉ/ስፖንሰር የማይደረጉ የተማሪ የጸሎት ቡድኖችን ጨምሮ በትምህርት ቤት ውስጥ ሃይማኖታዊ ልምዶቻቸውን ማካሄድ።

2. የተማሪዎች ሃይማኖታዊ ክለቦች ወይም የፀሎት ቡድኖች ሌሎች በትምህርት ቤት የማይደገፉ/ስፖንሰር የማይደረጉ የተማሪ ድርጅቶች ያሏቸው ተመሳሳይ መብቶችና ሃለፊነቶች አሏቸው።

3. ተማሪዎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መመሪያዎችን የሚያሟሉ ሀይማኖታዊ መዝሙሮችን ባካተቱ የበዓል የሙዚቃ ትርኢቶች/ኮንሰርቶች ላይ የመሳተፍ ወይም የመገኘት መብት አላቸው። በሚኖርበት ጊዜ፣ ተማሪዎች ሃይማኖታዊ ይዘቶች ላይ ውይይት ሊደረግበት በሚችል በሀይማኖታዊ ታሪክ ወይም ንፅፅር ጥናት ላይ በሚደረጉ ፈቃደኝነት ላይ በተመሰረቱ/ግዴታ ባልሆኑ ሴሚናሮች ላይ መገኘት ወይም መሳተፍ ይችላሉ። በነዚህ ትምህርቶች የሚቀርቡት በሃቅ የተመሰረቱና ያልተዛቡ የተወሰኑ ሃይማኖታዊ ተልእኮዎችን አስተያየቶችን የማያራምዱ መሆን አለባቸው።

4. ተማሪዎች ከቤተሰብ ሃይማኖታዊ እና/ወይም ሌሎች ልማዶች ጋር የሚጋጩ ቁሳቁሶችን ወይም ተግባራትን በሚያካትቱ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚከናወኑ ፓርቲዎች ወይም የነፃ ጊዜ ዝግጅቶች በመሳሰሉ ትምህርት ነክ ባልሆኑ እንቅስቃሴዎች/ተግባሮች ላይ ለመሳተፍ ካልፈለጉ ሊፈቀድላቸው ይችላል።

5. ነገር ግን፣ MCPS በሃይማኖታዊ እና/ወይም በሌሎች ተቃውሞዎች ምክንያት የሚፈለገውን ሥርዓተ ትምህርት ከመማር ወይም ሥርዓተ-ትምህርታዊ ቁሳቁሶችን ከመጠቀም ነፃ የመሆን ጥያቄዎችን ማስተናገድ አይቻልም።

J. ክበቦች፣ ቡድኖች፣ እና የተማሪዎች ድርጅቶች

1. በትምህርት ቤት የሚደገፍ/ስፖንሰር የሚደረግ

a) ተማሪዎች በክበቦች፣ ቡድኖች፣ እና የተማሪ ድርጅቶች የመሳተፍ መብት እና የመሳተፍ ችሎታቸው ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉ የቦርድ መመርያዎችና የ MCPS ደንቦችን ለይቶ የማወቅ ሃላፊነት አለባቸው።

b) ተማሪዎች አጠቃቀማቸው በትምህርት ላይ ወይም በት/ቤት መደበኛ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ጣልቃ እስካልገባ ድረስ በት/ቤት መገልገያዎች የተደራሽነት መብት አላቸው። ተማሪዎች ይህን ልዩ መብት ያለአግባብ እንዳይጠቀሙ ሃላፊነት አላቸው።

c) የተማሪዎች የመሳተፍ መብት በርዕሰ መምህሩ ወይም እንቅስቃሴውን/ተግባሩን ስፖንሰር በሚያደርገው አካል ሊገደብ ይችላል–

(1) የዲሲፕሊን ህጎችና ደንቦች ጥሰት፣

(2) አንድ ተማሪ ከሥነ ምግባር ወይም ከህጋዊ መመዘኛዎች ጋር በሚፃረር ሁኔታ ውስጥ በመሳተፉ፣ወይም የቦርድ ፖሊሲዎችን፣ የ MCPS ደንቦችን፣ እና በካምፓስ ውስጥ እና ከካምፓስ ውጪ ተገቢ የሆነ ስነምግባርን የሚመለከቱ ሥነሥርአቶችን ባለማክበር፣ የሚከተሉትን ግንዛቤ ውስጥ ካስገቡ በኋላ በክለብ፣ በቡድን ወይም በተማሪዎች ድርጅት ውስጥ የመሪነትን ቦታ ለመያዝ ካለው/ካላት ብቁነት ከተሠረዘ፦

(a) የተማሪ የበፊት ስነምግባር ግምገማ

(b) የይርጋ ጊዜ

(c) ከክስተቱ በኋላ የተማሪው(ዋ) ስነምግባር

(d) ተገቢ ሲሆን፣ ከተማሪዎች እና/ወይም የት/ቤት ማህበረሰብ አባላት የተሰጠ አስተያየት

d) በክለቦች፣ በቡድኖች፣ ወይም በተማሪዎች ድርጅቶች ውስጥ ለአመራር ቦታዎች ለመመረጥ ወይም ለመሾም የሚፈልጉ ወይም የአመራር ቦታ ይዘው የሚገኙ ተማሪዎች የሚከተሉት ሃላፊነቶች አሉባቸው –

(1) ለግብረገባዊ፣ ህጋዊ፣ እና ተገቢ ባህሪ አርአያ መሆን፣ እና

(2) ሁሉንም የቦርድ ፖሊሴዎችን፣ የ MCPS ደንቦችን፣ እና ሂደቶችን፣ በ MCPS ግቢ ውስጥም ይሁን ከግቢ ውጭ ማክበር።

2. በትምህርት ቤት የማይደገፉ/ስፖንሰር የማይደረጉ

የሚከተሉትን ሀላፊነቶች እስካሟሉ ድረስ ተማሪዎች ትምህርት በማይሰጥበት ጊዜ በትምህርት ቤት የማይደገፍ/ስፖንሰር የማይደረግ ስብሰባ የማካሄድ መብት አላቸው፡

a) ስብሰባው የደህንነት ወይም የፀጥታ አደጋ ስጋት የማያስከትል ከሆነ።

b) ስብሰባው በፈቃደኝነት የሚደረግ፣ በተማሪዎች ተነሣሽነት/አነሣሽነት፣ እና በት/ቤት ስፖንሰር ያልተደረገ ወይም በትምህርት ቤት ክለብ ያልተወከለ ከሆነ።

c) ስብሰባው በት/ቤት ወይም በትምህርት ሥርአቱ ሰራተኞች ስፖንሰር ያልተደረገ ቢሆንም ለደህንነት ሲባል በት/ቤት ሰራተኛ ቁጥጥር ሊደረግ ይችላል።

d) ማንም የት/ቤት ሰራተኛ እንደዚህ ያሉትን ስብሰባዎች አይመራም ወይም ንቁ ተሳታፊ አይ(ት)ሆንም።

e) ስብሰባው በት/ቤት ውስጥ በሚካሄዱ ትምህርታዊ ክንውኖች ላይ በጉልህ ሁኔታ ጣልቃ እንደሚገባ በቅድሚያ ሊተነበይ አይችልም።

f) የት/ቤቱ አባል ያልሆኑ ግለሰቦች የቡድን እንቅስቃሴዎችን አይመሩም፣ አያካሂዱም፣ አይቆጣጠሩም፣ ወይም በመደበኛነት አይከታተሉም።

g) ለሌሎች በትምህርት ቤት ለሚደገፉ/ስፖንሰር ለሚደረጉ ክበቦችና ድርጅቶች እንደሚደረግላቸው የስብሰባ ቦታ የመፍቀድ እና ለስብሰባዎች ማስታወቂያ ማስተላለፍያ የሚውል ቀላል ወጭዎችን ከመሸፈን ባሻገር ምንም የመንግስት ገንዘብ ወጪ አይደረግም።

K. ፀረ መድሎአድሎአዊነት

1. ተማሪዎች በእርስበርስ መከባበር እና በተመሳሳይ አግባብና በአክብሮት የመያዝ መብት ላይ በተገነባ መርኅ ራሳቸውን እንዲገዙ ሃላፊነት አለባቸው።

2. ሁሉም የጥላቻ/የአመፅ ድርጊቶች እና ህገወጥ መድልዎ ተቀባይነት የሌላቸው እና በቸልታ የማይታለፉ ናቸው፣በተለይም በቦርድ ፖሊሲ ACA ፣መድልዎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃት ላይ እንደተገለጸው በተጨባጭ ወይም በሚታዩ ግላዊ ባህሪያት ላይ የተመሠረቱ አድሎአዊ ተግባሮች ተቀባይነት የላቸውም።

3. በት/ቤት ስፖንሰር ያልተደረጉ የተማሪዎች ድርጅቶች የት/ቤት ደንቦች አፈፃፀምን በሚመለከቱ ውሳኔዎች እኩል እና መድልዎ የሌለው አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው።

L. አለባበስና አካልን ማስዋብ

1. ተማሪዎች አለባበሳቸውና የአካል ማስዋብ ለት/ቤት አካባቢ ተስማሚነት ያለው እና የት/ቤት አካባቢ የዲሲፕሊን መመሪያ በሚያከብር ሁኔታ የማድረግ ሃላፊነት ኣለባቸው።

2. ተማሪዎች፣ አለባበሳቸው ከዚህ በታች በክፍል 3 ከተገለፁት መስፈርቶች ጋር የሚስማማ እስከሆነ ድረስ፣ ከሀይማኖታቸው ጋር የተያያዘ ወይም ሃይማኖታዊ መልዕክትን የያዘ ልብስ ሊለብሱ ይችላሉ።

3. በሚከተሉት ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር ተማሪዎች በአለባበሳቸው ወይም ራስቸውን በመንከባከባቸው/በመሽቀርቀራቸው ምክንያት ብቻ የዲሲፕሊን እርምጃ አይወሰድባቸዋም፦

a) በትምህርት አካባቢ የሚያደናቅፍ ሁኔታ ሊያስከትል ይችል እንደሆነ፤

b) በትምህርት አካባቢ ያዘናጋል ከተባለ፤

c) የራስን ወይም የሌሎችን ጤንነት እና/ወይም ደህንነት አደጋ ላይ ይጥላል ወይም አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል ተብሎ ከታሰበ፤

d) አግባብነት ያለው የኮርስን ወይም የእንቅስቃሴ ግዴታን ማሟላት አያስችልም ተብሎ ከታሰበ፤

e) ከወንበዴዎች ጋር ግንኙነት ያለው አለባበስ ከሆነ፤

f) ባለጌ፣ ስድ፣ አፀያፊ፣ እርቃን የመሆን፣ ወይም ፍትወታዊነትን የሚያንጸባርቅ፣ ወይም

g) ትምባሆን፣ ማጨስን፣ አልኮልን፣ እፆችን፣ ወይም ወሲባዊ ማነሳሳትን የሚያስተጋባ ከሆነ።

M. የተማሪ ሪኮርዶች

ተማሪዎችና ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው የተማሪዎችን የተጠራቀሙ የት/ቤት ሪኮርዶች ይዘታቸውን ማብራራትና መተርጎም ከሚችሉ የሚመለከታቸው የት/ቤት ሠራተኞች ጋር በመሆን ኮንፈረንስ ላይ ባሉበት ወቅት የማየት መብት አላቸው። (የተማሪ ሪኮርዶች ጥበቃና አያያዝን ለማየት የሚቻለው MCPS ደንብ JOA-RA፣ የተማሪ ሪኮርዶች አጠባበቅና አያያዝ ድንጋጌ መሰረት ነው።

N. መፈተሽ እና መውረስ

ተማሪዎች፣ የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖቻቸው፣ ወይም በትምህርት ቤት ግቢ ወይም በትምህርት ቤት የሚደገፍ/ስፖንሰር የተደረገ ተግባር በሚካሄድበት አካባቢ የቆሙ መኪናዎች ስልጣን ባለው ፈታሽ አግባብነት ባለው የታመነ እና MCPS ደንብ JGB-RA፣ፍተሻ እና መያዝና መውረስ ላይ የተቀመጡትን ቅደም ተከተሎች በመከተል ፍተሻዎች ይደረጉባቸዋል።

O. ይግባኝ፣ የቅሬታ አቀራረብ፣ ህጋዊ አፈፃፀም

በዲሲፕሊን እርምጃ፣ በቅሬታ አቀራረብ፣ ወይም በአድልዎ ቅሬታ ተማሪዎች የፍትሃዊነት አያያዝ መብት አላቸው።[2] የዚህ አይነት አሠራር መኖሩን ለማረጋገጥ፣ የት/ቤት ህጎች ከቦርዱ ራእይ፣ ተልእኮ፣ ዋነኛ ዓላማዎች፣ እና ዋነኛ እሴቶች እና በሥራ ላይ ካሉት ህጎችና ደንቦች ጋር ተስማሚ መሆን አለባቸው።

MCPS ደንብ KLA-RA፣ ከህዝብ ለሚነሱ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ምላሽ መስጠት በሚለው ላይ እንደተገለጸው፥ተማሪዎች ልክ እንደሌሎች የህብረተሰብ አባላት ለሚሰማቸው ቅሬታዎች መፍትሄ የመፈለግ ተመሳሳይ መብቶች አሏቸው።

1. ተማሪዎች፣እንደነገሩ መፍትሄ ለማግኘት በመጀመሪያ ከርዕሰ መምህሩ፣[3] ወይም ሌላ የሚመለከተው አስተዳዳሪ ጋር እንዲነጋገሩ ይበረታታሉ።[4]

2. የተማሪ ቅሬታ ወይም አቤቱታ ኦፊሴላዊ ባልሆነ መንገድ ሊፈታ ካልቻለ፣ ተማሪዎች MCPS ደንብ KLA-RA እንደተደነገገው የቅሬታ ይግባኝ ከማህበረሰብ የሚቀርቡ ጥያቄዎችና አቤቱታዎች ምላሽ አሰጣጥ ድንጋጌ መሠረት የመጠየቅ መብት አላቸው።

P. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የተማሪ መብቶችና ሃላፊነቶች መመርያ ስርጭት

ተማሪዎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የተማሪ መብቶችና ሃላፊነቶች መመርያ ቅጂ የማግኘት መብት አላቸው።

1. በት/ቤት ውስጥ ይሰራጫል፤በተጨማሪም በየአካባቢው ት/ቤት ስርአት መሠረት ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ማህበረሰቡም ማግኘት ይችላሉ።

---

[2]MCPS በቦርድ ፖሊሲ ACA፣ አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃት ላይ እንደተደነገገው በተጨባጭ ወይም በሚታዩ ባህሪያት ላይ የተመሰረተ መድልዎን ይከለክላል ። አድልዎ ተፈፅሞብኛል በማለት ቅሬታ የሚያቀርቡ ተማሪዎች የተማሪ ደህንነት እና ስርዓት ማስከበር ክፍል አስተባባሪ የሆኑትን ሚስተር ግሪጎሪ ኤስ. ኤድመንድሰንን በዚህ አድራሻ፦ 850 Hungerford Drive, Rockville, Maryland 20850, 240-740-3215 ቢሮ ቁጥር 55፣ ወይም በዚህ ኢሜል SWC@mcpsmd.org ማግኘት ይችላሉ።

[3] የሚቀርበው የጾታዊ ጥቃት ቅሬታ በርእሰመምህር(ት) ላይ ከሆነ፣ ቅሬታው ፋይል መደረግ የሚገባዉ ለ..ይሆናል።ስርዓት የማስከበር እና የምርመራ ክፍል አድራሻ፦ Department of Compliance and Investigations, 45 West Gude Drive, Rockville, Maryland 20850, 240-740-2890 or DCI@mcpsmd.org.

[4]በፆታዊ ጥቃት ቅሬታ ምርመራ በሚደረግበት ወቅት፣አመልካቿ(ቹ) ከተከሳሹ(ሿ) ጋር ፊት ለፊት መገናኘት ወይም በምንም ሁኔት መጋጠም የለባቸውም።

2. ተማሪዎች እና ሰራተኞች በመመሪያው ላይ ስለተደረጉት ለውጦች እንዲያውቁ እና ተማሪዎች መብቶቻቸውን እና ግዴታዎቻቸውን እንዲረዱ እና እንዲያሟሉ ለመርዳት የካውንስሊንግ አገልግሎት መኖሩን እንዲገነዘቡ ማድረግ የርእሰ መምህሩ ሃላፊነት ነው።

3. ቢያንስ የመመርያው ቅጂ በርእሰመምህር ጽ/ቤት፣ guidance ቢሮ፣ እና በት/ቤት ሚድያ ማእከል መገኘት አለበት። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ውስጥ የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች መመሪያ ኤሌክትሮኒክስ ቅጂMCPS ድረ ገጽ ላይ ይለጠፋል እና MCPS ደንብ KBA-RC፣ ለአስፈላጊ ሰነዶች የሚደረግ የጽሁፍ እና የቃል ትርጉም ላይ የተቀመጡትን ሥርአቶችበማክበር ይተረጎማሉ።

***ተዛማጅ ሠነዶች፦*** Annotated Code of Maryland, Education Article 7-121, 7-308; Code of Maryland Regulations 13A.08.01.03 and 10; 09.12.23.01, A Student's Guide to Rights and Responsibilities in MCPS, Student Code of Conduct in MCPS, MCPS Guidelines for Respecting Religious Diversity, MCPS Guidelines for Students: Gender Identity

***የደንቡ ታሪክ፦*** አዲስ ደንብ ኦገስት 19,1994፣ ጁን 27, 1997 ተሻሽሏል፣ጁላይ 20, 1998 ተሻሽሏል፣ ሜይ 24, 2000 ተሻሽሏል፣የተሻሻሉ የጽ/ቤት ስያሜዎች፣ ጁን 1, 2000፣ ሜይ 23, 2002 ተሻሽሏል፣ ኤፕሪል 13, 2004 ተሻሽሏል፣ ጃንዋሪ 25, 2006 ተሻሽሏል፣ ጁን 27, 2007 ተሻሽሏል፣ ጁን 13, 2008 ተሻሽሏል፣ኦገስት 8, 2011 ተሻሽሏል፣ ዲሴምበር 19, 2014 ተሻሽሏል፣ ሴፕቴምበር 27, 2016 ተሻሽሏል፣መጠነኛ ክለሳዎች ጁላይ 24, 2017፣ ዲሴምበር 4, 2018 ተሻሽሏል፣ ኦገስት 09, 2021 ተሻሽሏል፣ኦክቶበር 23, 2023 መጠነኛ ክለሳ ተደርጎበታል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መግለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ:- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው:-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች:-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ።  በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ:- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው:-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው:-*** |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድእንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው:- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው:- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Well-being<br>Office of Well-being, Learning, and Achievement<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-5630 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው:-*** | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል:-
U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY);  Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር:- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ፌብሩዋሪ 2024